የኢትዮጵያ የፖለቲካ እስረኞች አንድነት ኮሚቴ (ኢፖእአኮ)

SOLIDARITY COMMITTEE FOR ETHIOPIAN POLITICAL PRISONERS (SOCEPP)


መስከረም 21/2007 (ኦክተበር1/2014)

# <u>ወገን ደረጀ በጋሻውን እንታደገው !</u>

<u>በዩጋንዳ መኖር የማልችልበት ሁኔታ ላይ እገኛለሁ።</u>

<u>ግልጽ ደብዳቢ---ህይወቴ አደጋ ላይ ወድቋል።</u>

ገጣሚና ጋዜጠኛ ፥የሰባዊ መብት ተሟጋች ደረጀ በጋሻው ከምን ግዜውም በላይ በስጋት ላይ መሆኔን ስጠቁም በቁም እስር ላይ እንዳለ ሰው እየኖርኩ መሆኔን ወገኖቼ ሁሉ እንዲገነዘቡልኝ እፈልጋለሁ። በሙያዬ በሰደት ሃገር ያቅሜን ለማበርከት በማሰብ ዜናና መጣጥፎችን በኢትዮጵያንሪቪው ላይ ፖስት ማድረግ ከታህሳስ ወር 2014 አጋማሽ ጀምሮ አቁሜያለሁ።አሁን በፌስቡክ ተውስኜ እገኛለሁ። በሳውዲ በወገኖቻችን ላይ የደረሰውን ሰቆቃ ለአለም ህብረተሰብ ለማሳወቅና ለማውገዝ ህዝባዊ ስብሰባ በማስተባበሬ የወያኔ ቆንስላ ከሶኝ በዩጋንዳ ከፍተኛ የፖሊስ ኮማንደሮች ከድርጊቴ እንድታቀብ ተነግሮኝ ጉዳዩን ለሰደተኞች ጉዳይ ቢሮና ለሰብዓዊ መብት ተከራካሪ ተቋማት አመልክቼ አርፌህ ተቀመጥ ተብያለሁ።

ስደተኛ በተሰደደበት ሃገርና በተጠለለበት ሃገር የፖለቲካ እንቅስቃሴ ማድረግ አይችልም።መጻፉንም አቁም የሚል ምክር አዘል ማስፈራርያ ደርሶኛል፡፡ ስደተኛው የራሱ ማህበር እንዲመሰርትም የበኩሌን በማድረጌ በአሳዳጅ ሃይሎች ወከባና ዛቻ እንዲሁም እግር በእግር ስለላ እየተደረገብኝ ከቦታ ቦታ ያለ ስጋት መዘዋወር የማልችልበት ሁኔታ ተፈጥሯል። ከባለቤቴ ጋር ያለምንም ስራና ገቢ የወገን ተረጂ ሆነን የUNHCR የሪሲትልመንት ውሳኔን በመጠበቅ ዕድሚያችን በከንቱ እየባከነና ሞራላችን እየተጎዳ ነው። ቤት በመቀመጥ ረጅም ስአት በማሳለፌ ጤናዬም እየተቃወሰና ክብደቴ እየጨመረ ነው።የሶስተኛ ሃገር የጥገኝነት ጥያቄዬም መልስ ሳያገኝ እየተንጓለለ ነው። ጉዳይህ ውሳኔ እየጠበቀ ነው። ጠረጴዛ ላይ ነው ያለው ከተባልኩ እንኳን 2 አመታት ተቆጠረ። በካናዳ ያሉ የሰባዊና የጋዜጠኞች መብት ተሟጋች ተቋማት ግሩፐ 5 የስፖንሰር ሺፕ ወረቀት ወይም ወደካናዳ ከለላ የማገኝበት ሁኔታ ቢመቻችልኝ መልካም ይሆናል እላለሁ።

እየጻፍኩ ያለስጋት የምኖርበትንና ለሃገርና ለወገን ጠቃሚ እንድሆን ወደ ሶስተኛ ሃገር በተቻለ ፍጥነት እንድሻገር የዘመቻ ስራ እንዲሰራልኝ በታላቅ ትህትና በልዑል እግዚአብሄር ስም እማጸናለሁ።

ደረጀ በጋሻው

የቀድሞ አስኳል ጋዜጣ ዋና አዘጋጅ

#የምስራቅ አፍሪቃ ስደተኛ

ጋዜጠኞች ማህበር ሊቀ-መንበር

#የኢትዮጵያን ማህበረሰብ በዩጋንዳ

የቦርድ አባልና ማህበራዊ ጉዳዮች ተጠሪ

#የካምፓላ መካነ ሰላም መድሃኒዓለም ደብር

መንፈሳዊ ሰበካ ጉባዔ ምክትል ሊቀ-መንበርና ረዳት ጸሐፊ

ዩጋንዳ


**INJUSTICE ANYWHERE IS INJUSTICE EVERYWHERESOCEPP, 30 RIGA COVE, WINNIPEG,MB R2P 2Z7,CANADA**

**E MAIL: SOCEPP @AOL.COM**

**WEB SITE: WWW.SOCEPP.CO**